

**የእጩ ስም:-** **Julie Kang (ጁሊ ካንግ)**
**የምርጫ ዘመቻ ስም:-** **Julie for Seattle D5 (ጁሊ ለሲያትል D5)**
**የምርጫ ዘመቻ ድህረ ገጽ:-** **https://julieforseattle.com/**
**የሥራ መደብ:-** **የከተማ ምክር ቤት ዲስትሪክት 5**
**የምርጫ ዘመቻ ስልክ ቁጥር:-** **206.880.3873**
**የእጩ መተዋወቂያ (የ200 ቃላት ገደብ):-**

የዲስትሪክት 5 የረጅም ጊዜ ነዋሪ፣ አስተማሪ፣ እና ንቁ የማህበረሰብ አባል ነኝ። በሰሜን ሲያትል ህይወቴን የገነባሁ ስደተኛ እንደመሆኔ መጠን፣ የከተማ ውሳኔዎች የሠራተኛ ቤተሰቦችን፣ ስደተኞችን፣ እና አነስተኛ ንግዶችን የዕለት ተዕለት ተግባራትን እንዴት እንደሚቀርጹ ተረድቻለሁ።

መሪዎቻችን እንዲያዳምጡን እና ዲስትሪክታችን በትክክል ምን እንደሚፈልግ እንዲረዱ እንፈልጋለን። ቅድሚያ የምሰጣቸው ነገሮች በተመጣጣኝ ዋጋ መግዛት መቻል፣ ተመጣጣኝ ዋጋ ያለው መኖሪያ ቤት፣ ደህንነት፣ እና ቤት አልባነት እና የስደተኞች ጥበቃዎች ናቸው።

ሙያዊ ሕይወቴን በሕዝብ እና በከፍተኛ ትምህርት አሳልፌያለሁ፣ ባለብዙ ቋንቋ ተማሪዎችን ለመደገፍ መምህራንን አሰልጥኛለሁ። በዩኒቨርሲቲ ኦፍ ዋሽንግተን እና በሲያትል ዩኒቨርሲቲ ሠርቻለሁ፣ ትላልቅ ፕሮግራሞችን በመምራት እና በመንደፍ፣ ውስብስብ የህዝብ በጀቶችን በማስተዳደር፣ እንዲሁም በተጠያቂነት፣ በፍትሃዊነት፣ እና በውጤቶች ላይ ያተኮሩ የተለያዩ የዘርፍ ሽርክናዎችን በመገንባት።

በሃለር ሌክ ማህበረሰብ ክለብ ቦርድ ውስጥ አገለግላለሁ፣ በምግብ ባንክ ውስጥ በፈቃደኝነት እሠራለሁ፣ ስደተኞች ማህበረሰባችንን አስተምራለሁ እና ህብረተ-ሰቡን ከ ICE በፊሽካ እና በሌሎሽ ነገሮሽ ለማንቃት እሰራለሁ፣ እና አነስተኛ ንግዶችን ለመደገፍ የFuseD5 የእግር ጉዞዎችን እመራለሁ። የWEA ዩኒየን ኩሩ አባል ነኝ እንዲሁም ባለቤቴ የUFCW 3000 አባል ነው።

ለከተማችን ምክር ቤት የማህበረሰብ እውቀትን፣ የባንክ ልምድን፣ የፖሊሲዎች እውቀትን እና አስተማማኝ አመራርን ይገቴ እመጣለሁ። ማህበረሰባችን የሚፈልገው ዓይነት መሪ ለመሆን ቃል እገባለሁ - ድምጽ ለሌላቸው ሰዎች የምታዳምጥና የምትሚገት ሰው።

የእርስዎን ድጋፍ ለማግኘት እና ዲስትሪክታችንን ለመወከል ክብር ይሰማኛል።

*ይህች እጩ በዲሞክራሲ ቫውቸር ፕሮግራም ውስጥ ተሳታፊ ናት።*



የዕጩ ስም፦ Nilu Jenks (ኒሉ ጄንክስ) የምርጫ

ቅስቀሳው ስም፦ Neighbors for Nilu (ኔበርስ

ፎር ኒሉ)

የምርጫ ቅስቀሳ ድረ-ገጽ፦
https://www.neighborsfornilu.org

የሥራ መደብ፦ City Council District 5 (የሲቲ ካውንስል ዲስትሪክት 5)

የምርጫ ቅስቀሳ ስልክ ቁጥር፦ 206-321-9890

North Seattle (ሰሜን ሲያትል) ልጆቼን እያሳደግኩ ያለሁበት፣ ከጎረቤቶቼ ጋር የቅርብ ወዳጅነት የመሰረትኩበት እና ማህበረሰቡ እንዲጠነክር ለረጅም ጊዜ የደከምኩበት አካባቢ ነው። በውሻ መናፈሻዎች ከሚደረጉ ጭውውቶች ጀምሮ የማህበረሰብ ስብሰባዎችን እስከመሳተፍ ድረስ ከጎረቤቶች ጋር መገናኘት እና ሰዎች እርስ በርሳቸው የሚረዳዱበትን ማህበረሰብ መፍጠር ደስ ይለኛል። ለዚህ አካባቢ ካለኝ ፍቅር የተነሳ በዝህ ምርጫ ላይ ዲስትሪክት 5ን ለማገልገል እወዳደራለሁ።

የኢራናውያን ስደተኞች ልጅ፣ የማህበረሰብ ተሟጋች እንዲሁም ሥራ የምትሠራ የሁለት ልጆች እናት ነኝ። ትምህርት ቤቶቻችንን ለማሳደግ፣ ሰፈሮቻችንን ይበልጥ ለማጠናከር እና ሁሉንም የሚያሳትፍ ማህበረሰብ ለመገንባት ከጎረቤቶች ጋር በመሆን ለዓመታት በትጋት ሰርቻለሁ።

በትምህርት ቤቶች፣ በመናፈሻዎች እና በትራንስፖርት አቅራቢያ ተመጣጣኝ ዋጋ ያላቸው መኖሪያ ቤቶች እንዲኖሩ በከተማው ምክር ቤት (City Council) ውስጥ ጠንክሬ እሰራለሁ። በቅርብ ጊዜ በተከሰቱት የግሮሰሪ እና የመድኃኒት ቤቶች መዘጋት ምክንያት በቤተሰቦች እና በአረጋውያን ላይ የደረሰውን የምግብ አቅርቦት ክፍተት ለመቅረፍ መፍትሄ እፈልጋለሁ። ለአየር ንብረት ፍትህ፣ ለተሻሻለ የትራፊክ ደህንነት እና ለበርካታ አስርት ዓመታት ቃል የተገቡልንን የእግረኛ መንገዶች ለመገንባት ቁርጠኛ ነኝ።

በFairVote Washington (ፌርቮት ዋሽንግተን) በነበረኝ ቆይታ፣ ዲሞክራሲያችን ይበልጥ እንዲጠነክርና እንዲጠበቅ የተለያዩ ማህበረሰቦችን በማስተባበር የበኩሌን አስተዋጽኦ አድርጌያለሁ።

ይህ የምርጫ ቅስቀሳ District 5 አብሮን የሚቆም፣ የሚያዳምጥና ውጤት የሚያመጣ አመራር ይገባዋል ብለው በሚያምኑ ጎረቤቶች ጉልበት የሚንቀሳቀስ ነው። እኔም ለማከናወን የወሰንኩት ይህንኑ ነው።

*እኚህ ዕጩ በዲሞክራሲ ቫውቸር ፕሮግራም ውስጥ በመሳተፍ ላይ ይገኛሉ።*